# የዳላስ ጉዞዬ

የጉዞዬ መንስኤ የ2004 ዓ ም በሰሜን አሜሪካ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል የሚደረገውን የእግር ኳስ ውድድር ለመመልከት ነበር።ከሥፍራው የተገኘሁትን ብቻ ሳይሆን ፤ከሐምሌ አንድ እስከ ሰባት የተደረገውን የእግር ኳስ ውድድር በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም ቀልብ ሰቧል።ሰለ ዝግጅቱ ስኬትና ድምቀት በመገናኛ ብዙሃን ብዙ ስለተባለ የምለው የለኝም።

ሆኖም በመክፈቻው ትርምስ ውስጥ የፌደረሺኑን ፕሬዘዳት አቶ ጌታቸው ተስፋዬን አገኝቼው እግዚሐብሔር ይስጥልኝ ለማለት እድል ገጥሞኛል። በኢትዮጵያውያን ወቅታዊ መወያይያ መድረክ (ECADF) የሰጠውን ቃል ምልስስ አንብቤ ሰለነበር ሰለእሱ መልካም ነገር ሰንቃለሁ። ዝግጅቱን ስምለከት ይህ ሰው ይህን ወጣት ትውልድ በአካልም፣ በመንፈስም በአእምሮም ገንብቶ የሃገር አለኝታ እንደሚያደርገው ተስፋዬን አጠናክሮልኛል። በአንዲት ደቃቃ ውስጥ ነበር ይህን ሁሉ ያልኩት።

በእስፓርቱ ውድድር ስም የሃገር ልጆች ከዓለም ዙሪያ  ሲገናኙ ታምር ሊፈጠር እንደሚችል መዘንጋት የለበትም። አልተነገረም እንጂ ይህ ፈደሬሺን ከተመሠረተ ብዙ ታምራት እንደተፈጠሩ አትጠራጠሩ።
እኔም በእስፓርት ሰም በዳላስ ጉዞዬ  ያገኘሁትን እኛነታችንን የሚገልጽ ልንከባከበውና ልናደርገው የሚገባ ታሪክ ላካፍላችሁ ወደድኩ።

ከቫኮበር ስያትል በመኪና  ከስያትል ፊኒክስ ከዚያም ወደ ዳላስ አይሮፕላን  ለወጥሁ፤ ዳላስ አይሮፕላን ጣቢያ 3፡30 ኤ ም ጠዋት ሰደርስ የእጅ ስልኬ አገልግሎቱን አቆመ።  ከሚቀበለኝ  የጓደኛዬ ወንድም  ተቆራረጥን፤ ከሃገር ሰወጣ በጣም ትንሽ ስለነበር የሚያውቀኝ አልመሰለኝም፤ ሽቅብ ቁልቁል ስል የባቱን ተራራ የሚያህል ጃዊሳ ሰሜን ሲጠራ በአሳንሳር ከሃኛው ፍቅ  ወለል ላይ ዱብ እንደልኩ ተሰማኝ። ከነሻንጣዬ  ተሸክሞ ከመኪናው ውስጥ  የጫነኝን ያህል ተሰማኝ። የሰላሳ ሰምንት ዓ መት ትዝታ መገለጫ መሆኑ ነው።



የዳላስ አውራ ጎዳና በዓለም የተነገረለት ነው። ዳላስ ሁሉ ነገር ጉዙፍ፣ ሰው፣ መንገዱ፣ ቤቱ፣ ምግቡ፣ የሥጋውን ቁርጥ አታንሱት ሆዳም እንዳትሉኝ አደራ፤ ኢሊያስ በዚህ ጉዙፍ መኪናው በተመቻቸው ጉዳና ላይ እየፈሰሰ በፍቅር ዜና ጀባ አለኝ፤ ሙዳውን ተቀበልኩ፤ ነጮች እንደሚሉት (He showered me with love news’  በዳለስ ስለሚኖሩ አንዳንድ ጓደኞቻችን ጠየኩት፣ እርሱ ትልቁ መሆኑ ነው፣ ‘ትንሹ ኢሊያስ ደግነቱን ልነግርህ አልችልም፣ ዳላስ ያለመኪና እስረኛ ነህ፤ ለአዲስ መጪዎች መኪና ገዝቶ የሚሰጥ ወንድም ነው፤ አብሐኪም ከአርባ በላይ ወገኖችን ሰፓሰር ያደረገ እንግዳ ተቀባይ ነው፤ ዶክተር አድማሱ ለኮሚኒቲው ጊዜውን የሰዋ በስፖርቱ ሥፍራ ድንኳን ተክሎ ስለጤና አጠባበቅ መግልጫ ሲሰጥ ታገኘዋለህ’ አለኝ። ዶክተር አድማሱን ከእድገት በሕብረት ዘመቻ ተመልሶ 1970 ዓ ም በአራት ኪሎ ግቢ በመስኩ ላይ ተጋድመን በወቅቱ ስለነበረው ቀውጢ ሁኔታ ከተወያየን በኋላ ጠፋሁበት። በስድስት ኪሎ በተፈጠረው ግርግር ከወጥመድ ገባሁ፤ ከዚያ በኋላ የት እንደደረስኩ አያውቅም። ከአብሐኪም 1968 ዓ ም ቤተሰብ ለመጠየቅ ከመደራችን የተያየን ነን፤ ትንሹ ኢሊያስ እንደ ትልቁ ኢሊያስ እርሱንም በስልሳዎቹ የተለየሁት ነበር።

ኢሊያስ ከሃገር ስዊድን ነበር ወደ ዳላስ የገባው። ስዊድን አብሯት የቆየው ዘመዱ የአብሮ አደጊ ዘመድ ከመሆኗ ሌላ በአንድ ላይ ይኖሩ ስለነበር ስለሷ ወገን ወዳድነትና ርህሩሕነት ይነግረኝ ስለነበር  ደግነቷ በዚያ የሕፃን አእምሮ  ውስጥ ተቀርፆ እስከ ዛሬ ይኖራል ። አጋጣሚዊን ሳገኝ ኢሊያስን ስለሷ ደህንነት ጠየኩት፤ እርግጥ በስልሳዎቹ መጨረሻዎች በአዋሳ ሁለተኛ ደረጃ ታስተምር እንደነበር ሰምቻለሁ፤ ከዚያ በኋላ የሆነውን አላውቅም። ለበጎ ያሰብነው አብዮት እንደጨው ዘር በታተነን፤ የዚህም ፈደሬሽን ተልኮዎ ተለያይተን እንደንቀር ይሆን? የፌደሬሽኑን ፕሬዘዳንት ስለዚህ የሚበረታታ ነው። አደራ ሁሉንም ነገር እርሱ ይስራው እንዳንለው፤ እኛም ድርሻችንን እንወጣ።



ኢሊያስ ስለእዚች እህት በጣም አስገራሚ ታምር አጫወተኝ፤ ትዳር መመሥረቷን ነገረኝ፤ ለሙሽራዎቹ የዳቦ ስም ሰጣኋቸው፤ ቡሩክታዊትና ተስፋ፤ ቡሩክታዊት አዲስ አበባ ትሄዳለች ከለውጡ በኋላ፤አሁን ከምትኅበኛት እህቷ ጋር አዋሳ ይኖሩ ነበር። እህቷም የአንደኛ ደረጃ አስተማሪ ነበረች። ቡሩክታዊት የነፃ ትምህርት አግኝታ ወደ ሶቪየት ሕብረት ትሄዳለች፤ ከዚያም ኮብልላ ከሃገር ስዊድን ትገባለች። ከብዙ ዓመታት በኋላ የደርግ መንግሥት ሲወድቅ ለጉብኝት ሃገርቤት ትሄዳለች፤ ታናሽ እህቷ የናፍቆቷን በአዲስ አበባ ከተማ ታሽራሽራታለች፤ የትራፊክ መብራት ያቆማቸዋል፤ ከመብራቱ ምሰሶ ሥር አንድ እናት የዕለት ጉርሳቸውን ይለምናሉ፤ ሠርተው እንደይበሉ የዓይናቸው ሕመም እንደአወካቸውም ይናገራሉ፤ ቡሩክታዊት ለእህቷ ‘እኚሕ እናት ትንሽ የሕክምና እርዳታ ቢሰጣቸው የሚድኑ ናቸው፤’ በማለት አስተያየቷን ትሰጣለች። መልሷን ሳትጠብቅ ‘በእህትነትሽ የምታደርጊልኝ ነገር ቢኖር እኚህን እናት ሆስፒታል ወስጄ ላስመረምራቸው እፈልጋለሁና በመኪናሽ ላይ አሣፍሪልኝ’ አለቻት። እህቷም የያዘችው መኪና ዘመናዊና ውድ ነበርና፤ ብዙዎች ይህን መሰል መኪና ያላቸው አንኳስ መንገድ ላይ የሚለምኑትን ወገኖች ሊጭኑ ቀርቶ የተጉሳቆሉ እናት አባታቸውን ዞር ብለው አያዩም፤ ሃገራቸውንም ቢሆን እንደዚያው ነው፤ ከጊዜ ጊዜ የምናየው ሐቅ ይህኑኑ ነው። ለዘመናት ከተለየች እህት ይህን መሰል ጥያቄ ሲቀርብ እንቢ ማለት እንዴት ይችላል? እኚህን እናት አሳፍረው ከጥቁር አንበሣ ሆስቲታል ወሰዷቸው፤ አስመዝግበው ካርድ አውጥተው የዓይን ባለሞያውን ሐኪም ይጠብቁ ጀመር። ተራቸው ሲደርስ የዓይን እስፔሻሊስቱ ገዋኑን ለብሶ ከተፍ ማለት፤ ብሩክታዊት ተስፋን ስታየው ተደወከች፤ እርሱም ብርክ ያዘው፤ ተስፋ ለብሩክታይት አዋሳ በነበረችበት ዘመን የከንፈር ወዳጇ ነበር፤ እርሷ ወደ ሶቭየት ስትሄድ እርሱም ወደ ኩቢያ ለትምህርት ተልኮ በዓይን ሕክምና ሰልጥኖ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ለዓመታት ሠርቷል። የመጀመሪያ ጥይቄው ‘ትዳር መሥረተሻል?’ የሚል ነበር፤ በሩክታዊት ‘አልመሰረትኩም’ ስትው ስሜቱን ለአንባቢው ልተው።

ብሩክታዊትም ጊዜዋን አራዝማ ከተስፋ ጋር ትዳር መሠረቱ። እኛን እናትም እስከ እልፍታቸው ተከባክበው ጦሯቸው። ዛሬ በሃገር ስዊድን ይናራሉ። አንድ ነገር ታዝባችኋል ስለሰው ጥሩ የሚያወሩ ሰዎች እራሳቸውም ጥሩ ሰው መሆናቸውን። ትልቁ ኢሊያስም ያ ሰው ነው።

ታደለ መኩሪያ
ቫንኮቨር ካናዳ
tadele@shaw.ca